# Barnebøker for Norge

barneboker.no

## እናንሲና ጥበብ

Skrevet av: Ghanaian folktale
Illustret av: Wiehan de Jager
Oversatt av: Mezemir Girma

Denne fortellingen kommer fra African Storybook (africanstorybook.org) og er videreformidlet av Barnebøker for Norge (barneboker.no), som tilbyr barnebøker på mange språk som snakkes i Norge.

Dette verket er lisensiert under en Creative Commons
Navngivelse 3.0 Internasjonal Lisens.
https://creativecommons.org/licenses/by/3.0/deed.no

# እናንሲና ጥበብ

Ghanaian folktale
Wiehan de Jager
Mezemir Girma
amharisk
nivå 3

(uten bilder)

በድሮ ዘመን ሰዎች ምንም አያውቁም ነበር። ሰብል እንዴት እንደሚዘራ፣ ሽመናም ሆነ የአንጥረኝነት ስራ እንዴት እንደሚሰራ ምንም ሃሳብ አልነበራቸውም። በሰማይ ያለው ንያሜ የተባለው አምላክ ግን የዓለምን ሁሉ ጥበብ ይዞ ነበር። በአንድ ገንቦም ውስጥ በጥንቃቄ አስቀምጦት ነበር።



መሬትም ላይ ወድቆ ፍርክስክሱ ወጣ። ጥበብም ለማንኛውም ሰው በእኩል ተዳረሰ። በዚህም ምክንያት ነበር ሰዎች እርሻ፣ ሽመና፣ አንጥረኝነትና ሌሎችንም ሰዎች መስራት የሚችሏቸውን ነገሮች ሁሉ የተማሩት።

ባጭር ጊዜም ከዛፉ ጫፍ ደረሰ። እዚያም ቆም አለና ‹‹ይህ ሁሉ ዕውቀት የኔ እንዲሆን ነው የተፈለገው፤ ግን ይሄው ልጄ ከኔ የበለጠ ብልህ ሆነ!›› በማለት አሰበ። አናንሲ በዚህ በጣም ተናዶ ያንን የሸክላ ገንቦ ከዛፉ ላይ ወደ ታች ወረወረው።



ከዕለታት አንድ ቀን ንያሜ ይህን የዕውቀት ገምቦ ለአናንሲ ለመስጠት ወሰነ። አናንሲ የሸክላውን ገንቦ ባየ ቁጥር አንድ አዲስ ነገር ያገኝ ነበር። ያስደስት ነበር!

ገብጋባው አናንሲ ‹‹ይህን ገንቦ በአንድ ትልቅ ዛፍ ጫፍ በጥንቃቄ አስቀምጠዋለሁ። ከዚያም ሁሉም የኔው ይሆንልኛል!›› ሲል አሰበ። አንድ ረጅም ክርም ገምዶ በሸክላው ገንቦ ዙሪያ አሰረ፤ ከዚያም በሆዱ ዙሪያ ጠመጠመ። ዛፉንም መውጣት ጀመረ። ገንቦው አሁንም አሁንም ጉልበት ጉልበቱን እየመታው ዛፍ መውጣቱ ከበደው።



ይህን ሁሉ ጊዜም የአናንሲ ትንሽ ልጅ ከዛፉ ስር ቆሞ እየተከታተለው ነበር። እሱም ‹‹አዝለኸው ብትወጣ አይሻልም ወይ?››አለው። አናንሲ ጥበብ የያዘውን የሸክላ ገንቦ ከጀርባው ለማሰር ሞከረ፤ እውነትም አመቺ ነበር።